# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 200 መጋቢት 6 2004 ገጽ 1


የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በደል እያደረሰ ቢሆንም በቂም ላይ የተመሠረተ ክፋቱ በአማራው ላይ ይበረታል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፀነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ ዘረኛ በሆነ መንገድ በአማራ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው በደልን አጥብቆ ይቃወማል። የወያኔን "ከፋፍለህ ግዛ" ፓሊስ ማስቆም የሚቻለው ራሱ ወያኔ ሲወገድ በመሆኑ ትግላችንን አስተባብረን በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ በጋራ እንዝመት ይላል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ተገፍተው ለባርነት ወደ አረብ አገር በሚላኩ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው ስቆቃ ቀጥሎበታል። በሊባኖስ አንዲት ኢትዮጵያዊ በአሰሪዋ በሚደርስባት ሰቆቃ ተማራ ህይወታን እንዳጠፋች ተዘገበ

ከወያኔ አገዛዝ ዘመን በፊት በአገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወደ አረብ አገር ለግርድና የሚላኩ ሴት እህቶቻችን ቁጥር በየጊዜው እያሻቀበ በሄደበት በአሁኑ ወቅት፤ በአሰሪዎቻቸው በሚደርስባቸው ወሲባዊ ጥቃት ስብ ዕናቸው የሚንኳሸሸው ፤ ዘግናኝ ድብደባ ተፈጽሞባቸው ለአካል ጉዳተኝነት የሚዳረጉ ፤የፈላ ዘይት ተደፍቶባቸው አካላታቸው የሚበላሸው፤ ከፎቅ ተወርውረው የሚገደሉና ፤ የሰሩበት የድካማቸው ዋጋ ሳይከፈላቸው ባዶ እጃቸውን በብረት ካቴና ተጠፍረው ወደ አገር ቤት የሚላኩ ዜጎች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ሰሞኑን በሊባኖስ አገር በአንዲት ኢትዮጵያዊት የቤት ሰራተኛ ላይ የደረሰው አሳዛኝ ግፍ አይነተኛ መረጃ ነው ሲል የግንቦት 7 ዘጋቢ ከመካከለኛው ምስራቅ በላከልን ዘገባ ገለጸ።

ዜጎችን በባርነት ወደ አረብ አገሮች በመላክ ከፍተኛ የሆነ የውጪ ምንዛሪ በማሰባሰብ ሥራ ላይ የተጠመዱት የወያኔ ንግድ ድርጅቶች ወደ ሊባኖስ ከላኩዋቸው ወጣት ሴቶች መካከል አለም ደቻሳ በተባለች ወጣት ላይ ባለፈው ሳምንት የተፈጸመው ድብደባ በድብቅ ቪዲዮ ተቀርጾ በመላው አለም ከተሰራጨ ቦኋላ ከፍተኛ ትኩረት መሳቡን የገለጸው ዘጋቢያችን በወጣቷ ላይ የደረሰውን ሰቆቃ እንደሚከተለው ገልጾአል።

ወጣት አለም ደቻሳ በአሰሪዋ ይደርስባት የነበረው ስቃይ ስለሰለቻት ባለፈው ሳምንት ከአሰሪዋ አምልጣ ቤይሩት ከተማ ወደሚገኘው የወያኔ ኤምባሲ ታመራና ስቃይዋን ለኤምባሲው ሰራተኞች ከገለጸች ቦኋላ ምንም እርዳታ ሊደረግላት እንደማይችል ተገልጾላት እያለቀሰች ስትወጣ አሰሪዋ ተከታትሎአት ኖሮ በር ላይ መኪናውን ይዞ ይጠብቃታል። ቤት ውስጥ እንደለመደው እንደሙብረቅ ይጮህባትና መኪናውን ወደአቆመበት ቦታ ከርሱ ጋር እንድትሄድ ያዛታል። ቤቱ በነበረቺበት ወቅት ከሚደርስባት መከራ የባሰ በአደባባይ ምንም እንደማያደርጋት እርግጠኛ የነበረቺው አለም እንቢ ስትለው አጅሬ ጭካኔ የተሞላበት ድብደባ ይፈጽምባትና እንደሌባ አንጠልጥሎ መኪናው ውስጥ ሊያስገባት ሲሞክር በመወራጨቷ በአካባቢው የነበሩትን ሰዎች ድጋፍ አስተባብሮ መሬት ላይ በመጎተት ሊያሳፍራት ሲሞክር በአካባቢው ከነበሩት አንዱ በስልኩ ላይ ባለው ቪዲዮ መቅረጫ ሁኔታውን ቀርጾ ኤልሲዲ ለተባለ ቴለቪዥን ጣቢያ ይልካ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በጋምቤላ ተማሪዎችን ይዞ ይጓዝ በነበረው አውቶቡስ ላይ ለደረሰው ጥቃት የወያኔ እጅ ሳይኖርበት እንዳልቀረ ምንጮች ገለጹ

በጋምቤላ ክልል ባለፈው ሰኞ መጋቢት 3 ቀን ተማሪዎችን ይዞ ይጓዝ በነበረው አውቶቡስ ላይ በተፈጸመው ጥቃት በድምሩ 19 ንጹሃን ዜጎች እንደተገደሉና ሶስት ሴቶች እንደተጠለፉ ከተዘገበ ወዲህ በጥቃቱ የወያኔ እጅ ሊኖርበት እንደሚችል በሰፊው እየተወራ መሆኑን በጋምቤላ ከተማ የሚገኘው የግንቦት 7 ዜጋቢ ገለጸ።

የፌደራል ልብስ የለበሱ ታጣቂዎች ጥቃት የፈጸሙበት አውቶቡስ ከጎዴሬ ተነስቶ ወደ ጋምቤላ ይጓዝ የነበረ እንደሆነ የገለጹት ምንጮች፤ አብዛኛው ተሳፋሪ እረፍት ላይ ሰንብተው ወደ ትምህርት ገበታቸው ይመለሱ የነበሩ የጋምቤላ ኮሌጅ ተማሪዎች እንደነበሩበትና ግዲያውን የፈጸሙ ታጣቂዎቹ ተሳፋሪዎቹን ሁሉ ከአውቶቡስ እንዲወርዱ ካዘዙ ቦኋላ በሆዳቸው እንዲተኙ ትዕዛዝ ሰጥተው ጭካኔ የተሞላበት የግዲያ እርምጃ እንደወሰዱባቸው ገልጸዋል።

የአካባቢው የወያኔ ባለስልጣናት ጥቃቱ ከተፈጸመ ቦኋላ አደጋው ወደተከሰተበት ጅዊ ከተማ የላኩት የፌደራል ፖልስ ተመሳሳይ ልብስ በለበሱ ታጣቂዎች ተኩስ ተከፍቶበት እንደነበረ የዘገበው ዘጋቢያችን፤ ካለፈው ጥር ወር ጀምሮ በጋምቤላ ክልል እያየለ የመጣው አመጽ በወያኔ አገዛዝ ላይ በፈጠረው ስጋት የጸጥታ ሰራተኞች ህብረተሰቡ አማጽያኑን ለማጋለጥ ፍላጎት የለውም በማለት ሲከሡ እንደነበር ጠቅሶአል። በዚህም የተነሳ የአመጽ እንቅስቃሴው ወያኔንና በክልሉ በህገወጥ መንገድ ነዋሪዎችን እያፈናቀለ መሬት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአወሊያ መስኪድን እንቅስቃሴ የሚመሩት የሀይማኖት መሪዎች በደህንነት ሀይሎች እየተዋከቡ መሆኑ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት ከትናትና በስቲያ እንደዘገበው፤ በአወልያ የተጀመረውን የሙስሊም ኢትዮጵያውያንን እንቅስቃሴ በበላይነት የሚያስተባብሩት መሪዎች ካለፈው አርብ ጀምሮ በደህንነት ሀይሎች እየተዋከቡ ከመሆናቸው በተጨማሪ የሙስሊሙን ጥያቄ ለአገዛዙ ለማቅረብ ከተመረጡት አንዱ የሆኑትን የኡስታዝ አቡበክርን መኪና 7 የወያኔ የደህንነት መኪኖች እየተከታተሉዋቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

የኡስታዝ አቡበከርን እንቅስቃሴ ለመከታተል በተመደቡ 7 የደህንነት መኪኖች ውስጥ በእየአንዳንዳቸው ከ2 እስከ 3 የሚደርሱ የደህንነት አባላት ነበሩ ያለው የኢሳት ዘገባ መኖሪያ ቤታቸውም በደህንነት ሀይሎች ተከቦአል ብሎአል።

ኢሳት ታማኝ የመረጃ ምንጮቹን ጠቅሶ ይፋ ባደረገው ዘገባው የሙስሊሙ ህብረተሰብ ተወካይ የሆኑትን ሰው መኪና ለመከታተል የተመደቡት የደህንነት መኪና ታርጋ ቁጥር ቶዮታ ኮሮላ አዲስ አበባ የጎን ቁጥር 2 ታርጋ ቁጥር 40674፣ 71580፣ 47376፣76847፣ ቶዮታ ቴራስ የጎን ቁጥር 2 ታርጋ ቁጥር 70478 እንዲሁም ኒሳን ሰኒ የጎን ቁጥር 3 አዲስ አበባ ናቸው።

ይህ የወያኔ እርምጃ ሙስሊሙ በመጪው አርብ በአወሊያ ተገኝቶ ተመሳሳይ ተቃውሞ እንዳያሰማ ከወዲሁ ለመከላከል ነው ተብሎአል ያለው ኢሳት አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ አስተያየት ሰጪ አሁን በሙስሊሞቹ ላይ የተከፈተው ወከባና ማስፈራሪያ በምርጫ 1997 ወቅት በቅንጅት መሪዎች ላይ ይደረግ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነው ማለታቸውን ዘግቦአል።

ሆኖም አገዛዙ ለሙስሊሙ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ እንደመስጠት በሀይልና በማስፈራራት ለመመለስ የሚያደርገው ሙከራ ሙስሊሙን ይበልጥ የሚያስቆጣና ወደ አልተፈለገ ብጥብጥ የሚወስድ ነው ሲል ኢሳት አስተያየቱን አክሎአል።

## ጥምረትና ኦነግ የተሳተፉት ደማቅ ህዝባዊ ስብሰባ በኖርዌይ ዋና ከተማ አስሎ ውስጥ ተደረገ

ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ በጄኔራል ከማል ገልቹ ከሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር በመሆን በአምስት አገሮች ውስጥ በሚገኙ 11 ከተሞች ህዝባዊ ስብሰባዎችን እያካሄደ መሆኑ ይታወቃል። ከእነዚህ ህዝባዊ ስብሰባዎች አንዱ ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 1 ቀን 2004 ዓ.ም በኖርዌይ ዋና ከተማ አስሎ ውስጥ በደማቅ ሁኔታ መካሄዱ ከስፍራው የደረሰን ዜና ያረጋግጣል።

በስብሰባው ላይ ኦነግን በመወከል የተገኙት የግንባሩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የውጭ ግኑኝነት ኃላፊ አቶ ቃሲም አባ-ናሻ ነበሩ። አቶ ቃሲም ኦነግ ረዥም ጊዜ ወስዶ ዓለም ዓቀፍና አገር አቀፍ ፓለቲካን መርምሮ በደረሰበት ውሳኔ መሠረት ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በመተባበር ፍትህና ዶ ሞክራሲና እኩልነት ለሰፈነባት ኢትዮጵያ በጋራ መታገል የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም የተሻለ ያስጠብቃል ብሎ በማመኑ በይፋ የአቋም ማስተካከያ ማድረጉ ለተሰብሳቢው አብስረዋል። ቀደም ባሉት ዘመናት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ከፍተኛ በደል መፈፀሙን አውስተው ከቀደመው ታሪክ ትምህርት ተወስዶ፤ ለወደፊቱ ተመሳሳይ በደል እንዳይፈፀም የሚያስተማምን ሥርዓት ዘርግቶ ወደፊት መጓዝ እንጂ ከእንግዲህ ኦነግ የታሪክ እስረኛ ሆኖ በአለፉ ነገሮች ላይ ብቻ በማትኮር ጊዜውን እንደማያጠፋ ተናግረዋል። "እኛ ዛሬ ይህንን ውሳኔ ስንወስን እያሰብን ያለነው የልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችንን ህይወት ነው። የኛ ልጆችና የልጅ ልጆች ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻቸው ጋር በእኩልነት የሚኖሩባት ኢትዮጵያ እንዲኖራቸው እንሻለን" ባሉ ጊዜ ተሰብሳቢው በከፍተኛ ጭብጨባ አድናቆቱን ገልጾላቸዋል።

ከእለቱ የመድረክ አስተናባሪዎች አንዱ የነበሩት የኦነግ የአዉሮፓ ተወካይ አቶ ዳባ ጉታማ "ኦሮሞ አይገነጥልም!!! በግድ ይገንጠል ከተባለም ሁላችንም አብረን እንገነጠላለን!!! አንገነጣጠልም" ባለ ጊዜ ተሰብሳቢ በረዥም ጭበጨባ ፉጨት ጭምር ደስታውን ገልጿል።

ቀጥሎ ሰፋ ያለ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት አቶ ዩሱፍ ያሲን ነበሩ። አቶ ዩሱፍ ያሲን ለብዙ ዓመታት በኢትዮጵያ የማኅበረሰብ ጥናት ያደረጉ ባለሙያ ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት በአፍሪቃ ቀንድ ፓለቲካ ላይ ትንተና ይሰጣሉ። በዚህ ስብሰባ ወቅትም አቶ ዩሱፍ የብሄተኝነትና የማንነት ስሜት እንዴት ሊመጣ እንደሚችል በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አስታከው ትምህታዊ ገለፃ ሰጥተዋል።

ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያን በመወከል የተገኙት ዶ/ር ታደሰ ብሩ የግንቦት 7 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ነበሩ። ዶ/ር ታደሰ ትብብርን በሚለከት ሰፋ ያለ ትንታኔዎችን ሰጥተዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የአማራን አርሶ አደር ለመታደግ ወያኔን ማስወገድ!!!

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በኢትዮጵያ ደሃ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ላይ ላይ የሚያደረሰው ግፍ ዝርዝሩ ብዙ ነው። በተለያዩ ቦታዎች የወያኔ ሠራዊት በአካል በመዝመት የፈጃቸው አርሶ አደሮች በሺህ መቆጠር ጀምረዋል። የወያኔ ኩባንያዎች የሚጫኑባቸውን የማዳበሪያ እዳ መክፈል እያቃታቸው ሺዎች ለእስራትና ለንብረት ዘረፋ ተዳርገዋል። በመቶ ሽዎች የሚቆጠሩ ደግሞ መሬታችሁ ከሩቅ አገራት ሃገራት ለመጡ ቱጃሮች ኢንቨስተሮች ይፈለጋል እየተባሉ ከቤታቸው ከእርሻቸው እየተፋነቀሉ የሃገር ውስጥ ስደተኞች ሆነዋል።

በተለያዩ አካባቢዎችና ወያኔ ባመቻቸው የዘር ፖለቲካ እየተጠለፉ አርሶ አደሮች እርስ በርሳቸው እየተጋጩ በርካታ ህይወት መጥፋት የጀመረው በወያኔ ዘመን ነው። የሃገሪቱ አርሶ አደር የወያኔ ጭሰኛ እንጅ ባለሃገርና ባለመሬት እንዳልሆነ እንዲሰማው ተደረጎ ከዛሬ ነገ ምን ይመጣብኝ ይሆን በሚል ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ወድቆ ህይወቱን መግፋት ከጀመረ ውሎ አድሯል።

ወያኔ ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በአማራ አርሶ አደሮች ላይ የሚፈጽመው ጥቃት የዚሁ የወያኔ ፀረ-አርሶ አደሮች መርሃ ግብር አካል ነው። ከሰሞኑ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች በሚገኙ የአማራ ተወላጅ የሆኑ ደሃ አርሶ አደሮች ላይ የሚፈጸመው ግፍ በአንድ በኩል በዚህ መነጽር የሚታይ ቢሆንም በሌላ በኩል ወያኔ በተለይ ለአማራ ህዝብ ካለው ስር የሰደደ ጥላቻና በቀል የሚመነጭ መሆኑን መዘንጋት አይገባም።

ባህር ተሻግረው የመጡ ቱጃሮች በሺዎች የሚቆጠር ጋሻ መሬት በነፃ ሲሰጣቸው ኢትዮጵያው ገበሬ ከአንድ የኢትዮጵያ ክፍል ወደ ሌላ የኢትዮጵያ ክፍል ሂዶ ለማረስ መሞከሩ “መጤ” ሲያስበለው፤ ለእንግልትና ሰቆቃ ሲዳርገው ማየትና መስማት እጅግ ልብን ይሰብራል።

በተለይም በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች ውስጥ በሰፈሩ የአማራ ዝርያ ባላቸውአርሶ አደሮች ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ እጅግ አሳሳቢ የሆነ ደረጃ ላይ ደርሷል። በርካታ የአማራ ተወላጅ የሆኑ ገበሬዎች በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች በተለያዩ ቦታዎች ለዓመታት ሲያርሱት የነበረው መሬት ተነጥቀው፤ “በነፍጠኛነት” ተዘልፈውና ተደብድበው፤ በብዙ ድካም ያፈሩት ጥሪት ተነጥቀው መባረራቸው እጅግ አሳዛኝ ጉዳይ ነው። ይህ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ብቻ አይደለም። ይህ የለየለት ዘረኝነት ነው።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ “መሬት የሚሸጠው በመቃብሬ ላይ” የሚለው ያለ ምክንያት አይደለም። መሬት ለመለስ ዜናዊ አማራንና የሚጠላውን ሁሉ ማጥቂያው፤ ወዳጆቹን ደግሞ መጥቀሚያ መሣሪያው ነው። መሬት ለመለስ ዜናዊ የሚሰጠው አገልግሎት ዘርዝሮ መጨረስ ቢያዳግትም አንዳንዱን ብቻ ለአብነት ያህል ብቻ እንጥቀስ።

1. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ “መሬት አይሸጥም” በሚለው ሰበቡ የኢትዮጵያን መሬት በሙሉ በእጁ በማስገባትነቱ ዘረኛ በሆነ መመዘኛው ለወገኖቹና ለአጨብጫቢዎቹ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን እየሰጠ በአንዲት ቅጽበት የሚሊዮኖች ብሮች ጌታ አድርጓቸዋል። በአንፃሩ ደግሞ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ የአማራ ገበሬዎች ለቤተሰቦቻቸው ቀለብ የሚሆን የጓሮ አትልክት መትከያ ቦታ አጠተው በረሃብ እንዲሞቱ እየተደረገ ነው።
2. አርሶ አደሩን ከረሃብ ለመታደግ በቀድሞው መንግሥት ትዕዛዝ በደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች ሰፍረው የነበሩ ድሃ የአማራ አርሶ አደሮች ዛሬ “በነፍጠኛ ሥርዓት” ርዝራዥነት እየተከሰሱ ስቃይ እንዲደርስባቸው እየተደረገ ነው።
3. አማራው ከአማራ ክልል ውጭ ብቻ ሳይሆን በአማራ ክልል ውስጥም ባይተዋር ተደርጓል። ጥንታዊውን የወልድባ ገዳም ግቢ ለስኳር ምርት በሚል በከበርቴዎች ዶዘር መታረስ ጀምሯል። ቦታው ከመታረሱ በፊት የአካባቢውን ገበሬ ይሁንታ የጠየቀ የለም። አቤት ለማለት የቃጡ አርሶ አደሮችና መነኮሳት በመለስ ዜናዊ ቅጥረኞች ተንገላተዋል።
4. የወልቃይት ጠገዴን ተወላጆችን መሬት በግድ በማስለቀቅና በማፈናቀል የትግራይ ተወላጆች ብቻ ተመርጠው እንዲሰፍሩበት ተደርጓል። በዚህም ምክንያት በሁለት አስር ዓመታት ውስጥ ብቻ የአካባቢው ነዋሪ የብሄረሰብ ስብጥር ሙሉ በሙሉ ተለውጧል።
5. ሰፊ የእርሻ መሬት ከአማራው ተነጥቆ ለሱዳን ተሰጥቷል። አባቶቻችንና እናቶቻችን ጦር አሰልፎ የመጣን ጠላት ተፋልመው ያቆዩልንን መሬት ለሱዳንና ከሩቅ አገራት ለመጡ ቱጃሮች ተሰጥቷል።
6. መለስና እኩይ ቡድኑ የኢትዮጵያን ሃብትም ተከፋለው ስለጨረሱት ለወጣቱ የተረፈው እዳ ብቻ ሆኗል። ለም መሬታችን ለባዕዳን በመሸጡ የገጠሩ ወጣት የሚያርሰው ቁራሽ መሬት እያጣ መሰደድ ከጀመረ ውሎ አድሯል። ወጣት ገበሬ ደቡብ አፍሪካ ድረስ ለመሰደድ ከቀዬው ነቅሎ የተነሳው በመለስ የአገዛዝ ዘመን ብቻ ነው። በገጠርም በከተማም የሚገኙ ወጣት ሴቶች ወደ አረብ አገራት ለመሄድ በረሃ ማቋረጥ፤ ባህርን በታንኳ መሻገር የጀመሩት በዚሁ የግፍ አገዛዝ ዘመን ነው። ዘመናዊ ትምህርት ያገኘው ወጣትም በተማረው ትምህርት አገሩንና ወገኑን የማገልገል ህልሙ ተጨናግፎ ስደት እጣ ፈንታው የሆነው በመለስ የአገዛዝ ዘመን ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በደል እያደረሰ ቢሆንም በቂም ላይ የተመሠረተ ክፋቱ በአማራው ላይ ይበረታል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፀነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ ዘረኛ በሆነ መንገድ በአማራ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው በደልን አጥብቆ ይቃወማል። የወያኔን “ከፋፍለህ ግዛ” ፓሊስ ማስቆም የሚቻለው ራሱ ወያኔ ሲወገድ በመሆኑ ትግላችንን አስተባብረን በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ በጋራ እንዝመት ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

................................................................................................................................

## ወያኔ የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር(አርዱፍ) ከቀናት በፊት ነጻ ያደረጋቸውን ሁለት ጀርመናዊያን ታጋቾችን አግቶ የቆየው የኤርትራ መንግሥት ነው የሚል የሃሰት ምስክርነት እንዲሰጡ በሽምግልና የተሳተፉት ሰዎች ላይ ጫና እየፈጠረ መሆኑ ታወቀ

በባለፈው ጥር ወር መግቢያ ላይ አፋር ውስጥ በወያኔ ታጣቂዎችና በአርዱፍ አማጽያን መካከል በተደረገርው የተኩስ ል ው ውጥ የአርታሌ እሳተ ገሞራን ለመጎብኘት ሥፍራው በነበሩ አምስት የውጭ ቱሪስቶች ከተገደሉ ቦኋላ በአርዱፍ አማፅያን ታግተው ለ2 ወራት ያህል የነበሩበት ትክክለኛ ቦታ ሳይታወቅ የቆዩት 2 ጀርመናዊያን ታጋቾች በአፋር ሽማግለዎች ድርድር መለቀቃቸው ይፋ በሆነ አጭር ቀናት ውስጥ የመለስ ዜናዊ ደህንነት ቢሮ በድርድሩ ላይ የተሳተፉትን የአገር ሽማግሌዎችን በመደለልና በማስፈራራት ሰዎቹን አግቶ የቆየው የኤርትራ መንግሥት ነው የሚል የሃሰት ምስክርነት እንዲሰጡ ግፊት እያደረገባቸው መሆኑን ታማኝ የሆኑ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ።

ከወያኔ ደህንነት ቢሮ አካባቢ ሾልኮ የደረሰን ይህ መረጃ እንደሚያመለክተው በሽምግልናው ከተሳተፉት የአፋር የአገር ሽማግሌዎች በተጨማሪ ድርድሩ ላይ የጀርመን መንግሥትን ወክሎ የተሳተፉ ዲፕሎማት ሳይቀር ይህንን የሃሰት መግለጫ በተሌቪዥን እንዲሰጡ ተጠይቀው እንደነበረና ግለሰቡ ፈቃደኛ ሳይሆኑ እንደቀሩ ለማወቅ ተችላአል።

የአገር ሽማግለዎቹ ጀርመናዊያኑ ዘጎች የታገቱት በሻቢያ እንደሆነ እንዲመሰክሩ ፤ በክልሉ የሚንቀሳቀሱትም አማጽያን እራሳቸውን አርዱፍ ነን የሚሉት በሃሰት እንደሆነና ኤርትራ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ የኤርትራ አፋሮች እንደሆኑ እንደሚያውቁ እንድናገሩ በየዕለቱ እየተወተወቱ እንደሆነ የገለጹት ምንጮች ሽማግለዎቹ በዕድሜም ጸና ያሉና በህብረተሰቡ ዘንድ የተከበሩ ስለሆኑ በቀላሉ ሊደለሉ እንዳልቻሉ አክለው ገልጸዋል።

የወያኔ የደህንነት ሰዎች ሽማግለዎቹን የማባበሉ ተግባር አሁንም እንደቀጠለ መሆኑን የገለጹት ምንጮች ምናልባት ጥረቱ ካልተሳካላቸው በጥቅምና በስልጣን በቀላሉ ሊደለሉ የሚችሉ ሌሎች ሰዎችን ፈልገው በቴለቪዥን ካሜራ ፊት እንዲናዘዙ ከማድረግ እንደማይመለሱ ግምታቸውን ገልጸዋል።
የታጋቾቹን በሰላም መለቀቅ አሰመልከቶ አርዱፍ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ፤ ሁለቱን ጀርመናውያን ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ ለአፋር ሽማግሌዎችና በኢትዮጵያ ለጀርመን ኤምባሲ ባለሥልጣናት ማስረከቡን ማስታወቁ ይታወሳል።

ባለፈው ጥር ወር በወያኔና በአርዱፍ አማጽያን መካከል ተደርጎ በነበረው የተኩስ ልው ውጥ ከተገደሉት አምስት ቱሪስቶች ሁለቱ የጀርመን፣ሁለቱ የኦስትሪያና አንዱ የሀንጋሪ ዜጋዎች ሲሆኑ፤እስካሁን ድረስ ለግድያው ሀላፊነቱን የወሰደ አካል ወይም ቡድን አለመኖሩ ይታወቃል።

በኢትዮጵያ የጀርመን ኤምባሲ ባለፈው ሳምንት በሰጠው መግለጫ፤ የኤምባሲው ባለሥልጣናት ከአካባቢው የአገር ሽማግሌዎች ጋር ባደረጉት ድርድር በአርዱፍ ታግተው የቆዩት ሁለቱ ጀርመናውያን ቱሪስቶች መለቀቃቸውን አስታውቆ እንደነበረ አይዘነጋም።

# የእሳት እራት

## ትውስታየ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር

(ክፍል 4 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ)

ህወሃቶች ወንጀል የሚሉት ቅንጅትን መደገፍ ነው። ወንጀል ሁኖ የሚቆጠረው የመንግስትን ከንቱ ፕሮፓጋንዳ አለማመን ነው። ወንጀል ሁኖ የሚቆጠረው ተውኝ እንደሰው ላስብበት ማለት ነው። ይህን የመሰለውን ነገር ነው እርሱ "እንዲህ ብሏል እርሷም እንዲህ ብላለች" እያሉ አሳብቀው እንዲባረር የሚያደርጉት። አንዱ የተባረረበት ምክንያት "መለስ መላጣ" ብሎ ተሳድቧል ተብሎ ነው። እስኪ እግዜር ያሳያችሁ የመለስን መላጣነት ራሱ መለስ ይክደዋል ?መለስ መላጣ ነው ማለት ምን የሚሉት ስድብ ነው? እልቁንስ ስድብ የሚሆነው ስለ መለስ ቅንድብ ማማር መዝፈን እንጂ ስለመላጣነቱ መናገር አልነበረም። ምክንያቱም የመለስ ቅንድብ የሂትለርን ይመስላል እንጂ አያምርም።

አሁን በየኢምባሲው የምናያቸው ዲፕሎማት ተብየዎች አብዛኛዎቹ ለህወሃቶች ወሬ በማቀበል ወንድሞቻቸውን አሳልፈው የሰጡ ሞራለ ቢስ ግለሰቦች ናቸው። ለዚያ ነውር ተግባራቸው ሽልማት ይሆናቸው ዘንድ በየኢምባሲው ዲፕሎማት ተብለው ተሹመዋል። እነርሱም ካራባታቸውን ሸብ አድርገው ሰው መሃል ሲቆሙ ወንድምና እህቶቻቸውን አሳልፈው በመስጠታቸው የመጸጸትና የማፈር መልክ አያሳዩም።

ምንም እንኳ እንዲህ በስውር እየተጠሩ በወንድምና እህቶቻቸው ላይ መረጃ እንዲሰጡ የሚጠየቁ ግለሰቦች ስም ዝርዝር በሚስጥር ይያዛል ቢባልም በተለያየ መንገድ ማን በማን ላይ ምን እንደመሰከረ እንዲያውቅ ይደረጋል። እንዲህም በማድረግ በጓደኞሞች መካከል ጥላቻን ተከሉ። ህወሃቶች አገርን ለማፍረስ የሚጠቀሙት የታወቀው አንዱ ዜዴያቸው ይሄው ነው። ክፉ መንግስት እንዲህ በወንድማማቾች መካከል ጥላቻን ይዘራል።

ይህ ተሰውሮ የሰራተኛውን ማንነት ሲሰልል የከረመው ቡድን አጥንቶ 42 ሰራተኞችን መርጦ እንዲባረሩ አስወሰነ። እያንዳንዱ ተባራሪ ቅሬታ አለኝ ካለ ግን ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተብሎ ለተቋቋመው ኮሚቴ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል ሲባልም ተነገረ። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ተብለው የተሰየሙት የሚከተሉት ናቸው።

| | |
|---|---|
| አምባሰደር ሃሊማ መሃመድ(አሮሞ) | አምባሳደር ግርማ አማረ(አማራ) |
| አቶ ዋህደ በላይ(ትግሬ) | አምባሰደር አማን ሃሰን(አሮሞ) |
| አቶ ምንሊክ ዓለሙ(አማራ) | አቶ ዮሃንስ አብርሃ(ትግሬ) |
| ወ/ት ፍርዶሳ አብዱልቃድር(ትግሬ) | |

እነዚህ ግለሰቦች ቅሬታ ሰምተው ችግሩን ለመፍታት ለእውነት ለመቆም ሃሞት ያላቸው ግለሰቦች አይደሉም። እንዲያውም የመንግስትን ፖሊስ የተቃወመ ሁሉ መባረር አለበት ብለው የሚያምኑ ናቸው። በሁለቱ ትግሬዎች ላይ መፍረድ አይቻልም። እነርሱ የታሰሩበት የጎሳ ሰንሰለት አለ። የሌሎቹ ግን ነውራቸው ክብራቸው የሆናቸው ሆዳም የሚባሉ ናቸው። ምኒልክ ዓለሙ ከዚያ በኋላ አምባሳደር ተብሎ ተሹሟል። የሚፈልገውም እርሷን ሹመት ነበር አግኝቷታል። ሌሎቹ ግን ቀድመው አምባሰደር ተብለው የተሾሙ ሲሆኑ ህወሃቶች አማራውንና አሮሞውን ለማሰቃየት የሚጠቀሙባቸው ብትሮች ናቸው። ሃሊማ መሃመድን "ከዚህ ቀደም አምባሳደር ያልንሽ በስህተት ነበር ካሁን በኋላ ተራ ዲፕሎማት ሁነሽ ትኖሪያለሽ" ብለዋት ከአምባሳደርነት ወርዳ ተራ ዲፕሎማት ሁና እየኖረች ነው።

እኔ የተባረርኩበት ደብዳቤ ሲደርሰኝ ቅሬታ አለኝ አልኩና ወደ እነዚህ ሰዎች ሄዱኩ። ከሳሼ ማነው ብየ ስጠይቅ ሚስጢር ነው አይነገርም አሉኝ። እሽ ጥፋቴ ምንድ ነው አልኩ ? ጥፋትህ መንግስትን ትቃወማለህ። በመንግስትም ፖሊሲዎች ላይ እምነት የለህም። እንዲያውም የጠቅላይ ሚንስትሩን የአመራር ችሎታ ታናንቃለህ አሉኝ። ለምሳሌ ጠቅላይ ሚንስትሩ ባድመ ላይ ያሳዩትን አቋም አንቋሸሃል አሉኝ። ምን ማለት እንደሆነ አልገባ አለኝ። ዝም ብየ እንዲህ ዓይነት ወሬ ከየት እንዳገኙ ማሰብ ያዝኩ። በእድሜው አባቴ ለመሆን ዘመን ያለው የቢሮየ ተጋሪ ጋር እንዲህ ያለ ነገር መነጋገሬ ትዝ አለኝ። እንዴት እኔን የሚያህል ልጅ ወልዶ አሳድጎ ሲያበቃ እንዲህ ዓይነት ትኝሽ ነገር አምጥቶ እኔን ለማስባረር አጉልቶና አዳብሮ ለመጠቀም ልቡ ጠነከር እያልኩ ሳስብ ዘለግ ያለ ግዜ ወሰድኩ። በባድሜ ጉዳይ ስንነጋገር "በአመራሩ ችሎታ ላይ ጥርጣሬ አለህ እንዴ" ብሎ የጠየቀኝ ቢሮየን የሚጋራኝ የህወሃቱ ሰው ነበር። በጣም ተገርሜ ሳበቃ እኔ በአመራሩ ላይ ጥርጣሬ የለኝም ስል ዋሸሁ። እነርሱም አላመኑኝም። በአመራሩ ብቃት ላይ ጥርጣሬ እንዳለህ በቂ መረጃ አለን። እንዲህ ዓይነት ጥርጣሬ ይዘህ ለመቀጠል አስቸጋሪ ስለሚሆን በዚህ ይብቃን አሉኝና አሰናበቱኝ። ከዚያም በገዛ አገሬ ይሄን ተናግረሃል ተብየ ከመባረሬ በላይ በሰብቅና የገዛ አገሩን ዜጎች በመሰለል ላይ የተመሰረት ደካማ መንግስት አገሪቷን እየመራት መሆኑ አሳዘነኝ።

ከዚያም ወደ ቢሮየ መሄድ ወደ ሲኦል የመሄድን ያክል ተሰማኝ። ሰው ካራጁ ጋር እንዴት አብሮ ይቀመጣል ?ይህ ቢሮየን የሚጋራኝ ሰው መሳይ አውሬ ያን ሁሉ ሲለፈልፍ የነበረው ወሬ ከእኔ ለመልቀም መሆኑን አሁን ተከሰተልኝ። ያችን ትንጥየ ክርክር ወስዶ ሲነግራቸው ትንሽም ቅር አለመሰኘቱ ገረመኝ። ይህ ሰው እኔን የሚያክል ልጅ አለው። እኔ እድሜየ ሃያ ሰባት ዓመት ሲሆነኝ እርሱ ከሃምሳ ዓመት በላይ ነበር። ከሃይማኖቱም ከእድሜውም ያላተማረ ክፍ ጨካኝ መሆኑን ሳስብ ሰይጣን ስጋ ለብሶ ቢሮየ ቁጭ ያለ መሰለኝ። ከሰይጣኑ በላይ ግን አገሪቷን የሚመሩት እንዲህ ዓይነት ምንምንቴ ሰዎች መሆናቸውን ሳስብ ከልቤ አለቀስኩ።

የህወሃትን እውነተኛ መልክ ዘረኝነቱን፤ ሌብነቱን፤ ሴሰኝነቱን፤ አገር አጥፊነቱንና ስግብግብነቱን ብነግረው ኑሮ በአገር ክዳትና በዘር ማጥፋት ወንጀል አስከስሶ የሞት ፍርድ እንደሚያስፈርድብኝ አሁን ገባኝ። የጠላትነት ፍጻሜው ይሄው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ጠላቴ ካልሆነ ሌላ ማን ጠላቴ ሊሆን ነው ስል ከራሴ ጋር ሙግት ያዝኩ። አሁን ይሄን ግለሰብና ድርጅቱን ብጠላ ምኑጋ ነው ስህተት የሚሆነው? እንደምንስ ሆኖ ልወደው ወይም ደግሞ ስሜት አልባ ልሆን እችላለሁ?

ወደ ቢሮየ ገብቼ ይህን ምናምንቴ ግለሰብ ሳይ እገድለው ዘንድ በልቤ አሰብኩ። ሰውነቴ ሁሉ በበቀል ስሜት ተወጠረ። ይህ ሰው ተስፋየን ገድሎታል። ምኞቴንም አምክኖታል። የእኔን ህልም አምክኖ እርሱ እንዴት ነጹህ አየር እየተነፈሰ ይኖራል!? አይደረግም ስል ለራሴ ነገርኩት። እናም ይኖር ዘንድ አልፈቀድለትም እያልኩ ከራሴ ጋር እየተሟገትኩ ብሮየ ደርስኩ።

ያ ክፉ ሰው ከብሮየ የለም። ብቻየን ተቀምጬ ህወሃት በመሆንና ባለመሆን መካከል ያለውን ልዩነት ሳሰላስል ቆየሁ። እነዚህ ሰዎች ትግሬዎች ናቸው ወይስ ሌሎች ስል ከራሴ ጋር ሙግት ያዝኩ? እነዚህን ሰዎች መቸ ነው ትግሬ ሁሉ ተሰብስቦ ወክሉን ያላቸው?። ለማንኛውም ድሮ እኛ የምናውቃቸው እነዚህያ ጠንካራ ሰራተኛ፤ ግልጽ፤ ውሸት የማያውቁ፤ ሃይማኖተኛ እና አልፎ አልፎ ግልፈተኛ ትግሬዎች ዛሬ የሉም። በዚያ መልክ የምናውቃቸውን ትግሬዎች እወክላለሁ የሚል አንድ ቡድን እንዴት እንዲህ በገዛ አገሬ እንዳልኖር ይከለክለኛል እያልኩ በሃሳብ ባዘንኩ። ሂሊናየን የሚያሳርፍ መልስ ግን ላገኝ አልቻልኩም።

ከሳሹና መስካሪው በሚስጢር ተይዞ 42 ሠራተኞች ጥፋተኛ ተብለው እንዲባረሩ ተደርጎ ጠማቸውን ማደረ የጀመሩት የትግሬ ነጻ አውጪዎች ነን በሚሉ ሃይሎች ነው። የእነዚህ ተባራሪ ወገኖች እውነተኛው ጥፋታቸው እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ ፍላጎት ማሳየታቸው ብቻ ነበር። ሌላ ጥፋት ሌላ የስነምግባር ጉደለት የሌለባቸው ንጹሃን በእውቀታቸውም በስነ-ምግባራቸውም እንከን የማይወጣላቸው የአገሪቷ ልጆች ነበሩ። ግና ምን ያደርጋል ተባረሩ። በአገሪቷ ውስጥም ሰርተው እንዳይበሉ የሥራ መልቀቂያ እንዳያገኙ ተፈረደባቸው።

እኔም ጥፋተኛ ተብየ ከተባረርኩ በኋላ የሥራ ልምዴን የሚገልጥ ደብዳቤ እንዲሰጠኝ ስጠይቅ "በገዛ ፈቃዴ ሥራየን ለቅቄአለሁ" ብለህ አመልክትና እንጽፍልሃለን ብለው በበደል ላይ በደል ፈጸሙብኝ። መባረሬ በደል ነው። ካባረሩኝ በኋላ ሌላ ቦታ ሰርቼ እንዳልኖርበት ማድረግ ግን ከበደል በላይ ሁኖ ሮሮ ሆነብኝ። ለማን አቤት ይባላል? ሁሉም ቦታ እነርሱ ናቸው። ከእነርሱ ጋርም ያሉ በርካታ ሆድ እንጂ ሂሊና የሌላቸው ብዙ ሌሎች አሉ። ለምንም የማይሆኑ ። እንዲህ ብቻየን በሃሳብ ስናውዝ መለሰ ተ/ማሪያም የተባለውን የመሥሪያ ቤቱን ባልደረባ አገኘሁት።

መለሰ ተ/ማሪያምና እኔ የአንድ ዓመት ምሩቃን ነን። እርሱ በስነ-ጽሁፍ ተመርቆ ውጭ ጉዳይ ፕሬስ መምሪያ ውስጥ ይሰራል። እኔና እርሱ የምንካፈለው የጋራ ነገር አለን።

ጠላ እየሸጡ ያስተማሩትን እናቱን ለመርዳትና ኑሯቸውን ለመቀየር ቤታቸውንም ለመሥራት ያለውን ምኞት ይዞ ውጭ ጉዳይ መሥራት ከጀመረ እነደ እኔ አራት ዓመት አልፎታል። እርሱም እንደ እኔ ዳቦ በሙዝ ተመግቦ ተመስገን ብሎ መኖርን ልማዱ ያደረገ ነበር። ሆኖም ግን ምኞቱን እውነት ሳያደርግ ከ42ቱ ተባራሪዎች መካከል አንዱ አደረጉት። እርሱም እንደ እኔ ነገሩ ሁሉ ግራ ገብቶታል።

አንተም እንደ እኔ የእሳት ራት ሆንክ ሲል ጠየቀኝ።

አዎን የእሳት ራት ሁኜያለሁ።

መለሰ ተ/ማሪያም ከእኔ በላይ ተስፋ ቆርጧል። "በዚህ ዓለም ከእነዚህ ሰዎች ጋር መኖር አያስፈልግም። እዝህ መሥሪያ ቤት በመሥራቴ ያተረፍኩት ፀፀት እንጂ ተስፋ አይደለም። ተስፋው የሞተ ሰው ያው የሞተ ነው። በሥጋው ቢኖርም ያው እንደሞተ ነው። እንድኖር ያደረገኝ አንድ ተስፋ ነበር። አሁን ያ ተስፋ ሙቷል። አልቋል። ተፈጽሟል። ከእነዚህ ሰዎች ጋር መኖርና መሥራት ሥቃይ ነው የሆነብኝ። ሁል ግዜ መሠቃየት ደግሞ ይታክታል" አለ በአሮጌ ጫማው የሚደፈጥጣትን አንዲት ትንሽ ጠጠር ወደ ታች ወደ ውስጥ ይበልጥ እየደፈቃት።

ምን ማለቱ እንደሆነ የገባኝ ከውጭ ጉዳይ ከተባረረ በኋላ አሰላ ሂዶ ከሚስኪን እናቱ ቤት ራሱን ሰቅሎ መሞቱን ከሰማሁ በኋላ ነው። መለሰ ተ/ማሪያም ጥሩ አንባቢ ጸሃፊና አስተዋይ ሰው ነበር። ለዚህ ጎበዝና ጥሩ ጸሃፊ ልጅ መሞት ሃላፊነቱን የሚወስዱት የመስሪያ ቤቱ የብአዴኑ ተወካይ ዘሪሁን ረታ አሁን አምባሰደር በሎሳንጀለስ ፤ተቀዳ ዓለሙ፤እና ህወሃት የተባለው ድርጅት ነው። ሆድ አደሮቹ ዘሪሁን ረታና ተቀዳ ዓለሙ አማራ ሁነው በአማሮች ላይ እንዲህ ዓይነት ህገ-ወጥ ድርጊት ሲፈጸም ቀንደኛ አስፈጻሚ ሁነው እየሰሩ ነው። እነዚህ ሰዎች "አማራ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው" ተብሎ በህወሃት የተጻፈውን ሰነድ አላነበቡም ማለት አይቻልም። በደንብ አንብበዋል ግን እንዲህ ዓይነት ነውር ከሆዳቸው አይበልጥባቸውም።

ተቀዳ በሦስቱ ሥርዓቶች የሠራ ነው። የእርሱ እድሜ ያላቸው "ፋኖ ተሰማራ እንድ ሆች ሚን እንደ ቼ ጉቬራ" ብለው ሲነሱ ተቀዳ ለንጉሱ ታማኝ ሁኖ ይሰራ ነበር። ደርግም መጥቶ ገንጣይ አስገንጣይ እያለ ሲፎክር አብሮ ይፎክር ነበር። አሁን ደግሞ ከህወሃት ጋር ሁኖ ደርግን እያማ የመ/ቤቱ ጌጣ ጌጥ ሁኖ አለ። አንድ ግዜ ሚንስቴር ዴኤታ ሌላ ግዜ ደግሞ ወርዶ አምባሳደር ሁን ሲሉት እየሆነ በከተቱት ሰገባ ውስጥ ሳይጨንቀው እየገባ የሚኖር ግለሰብ ነው። ይህ ግለሰብ ምኞቱ እስካልተጓደለ ድረስ ግድየለውም። ከስዩም የተራረፈውን እየለቃቀመ ደርግን በሃሜት ደሙን እየጠጣ ይኖራል። "አማራ የትግሬ ጠላት ነው" ሲሉትም "እውነት እኮ ነው" እያለ ኑሮውን ይኖራል እንጂ ሌላ አይናገርም። (ክፍል 5 ሳምንት ይቀጥላል)

## የኢትዮጵያው አገዛዝ ባወጣቸው አፋኝ ህጎች ምክንያት በአገሪቱ ውስጥ ለሰብ አዊ መብት ጥበቃ መሥራት ከማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሶአል ሲል አምንስቲ ኢንተርናሽናል መግለጫ አወጣ

የወያኔ አገዛዝ ባወጣቸው የተለያዩ አፋኝ ህጎች የተነሳ የሰብ አዊ መብቶች ጥሰትን ለመከታተል በአገሪቱ ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ 2 ድርጅቶች ምንም አይነት ሥራ ለመሥራት ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ሲል ታዋቂው አለም አቀፍ የሰብ አዊ መብት ተሟጋች ድርጅት አምንስቲ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያን አስመልከቶ በትናንትናው ዕለት ባወጣ ባለ 38 ገጽ ሪፖርት አጋለጠ።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ማህበራት እንቅስቃሴ ለመገደብ የወጣው አዋጅ ቁጥር 5/2003 እንዲሁም በቅርቡ የወጡት የጸረ ሽብር ህግና የሚዲያ አዋጆች የመብት ተሟጋቾችን በቀላሉ ለመወንጀል የሚያስችሉ ልቅ ትርጎሞች ስላላቸው በመስኩ የተሰማሩ ሰዎች ነጻ ሆነው ሥራቸውን እንዳይሰሩና በፍርሃት ተሸማቀው አፋቸውን እንዲዘጉ አድርጎአቸዋል ብሎአል የአምንስቲ ሪፖርት።

በአፍሪካ የአምንስቲ ምክትል ዳይሬክተር የሆኑት ሚካኤል ካጋሪ እንደተናገሩት ዜናች በጸጥታ ሠራተኞች ወከባና ጥቃት እየተፈጸመባቸው ፍዳቸውን እያዩ ባለበት በአሁኑ ወቅት መንግሥት የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ሥራቸውን እንዲሰሩ ሁኔታውን እንደማመቻቸት ፋንታ በተለያዩ አፋኝ ህጎች እንዲሸመደመዱ አድርጎአቸዋል በማለት ከሰዋል።

## በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ተገፍተው ለባርነት ወደ አረብ አገር በሚላኩ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አለም በአሰሪዋና በተባባሪዎቹ በተፈጸመባት ድብደባ ላሌ አግዳሚውን የሰቀጠጠ የስቃይ ጩኼት ስታቀልጥ ብሶቷን አድምጦ መፍትሄእ ለመስጠት ያልፈቀደው የአገሯ ኤምባሲ ከቢሮ ወጣ ብሎ ለምን ያንን የመሰለ ሰቆቃ በቢሮው ደጃፍ ላይ በአገሩ ዜጋ ላይ እንደተፈጸመ ለመጠየቅ ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቶአል ብሎአል ዘጋቢያችን። የ ኤል ሲ ዲ ተሌቪዥን በአለም ደቻሳ ላይ የተፈጸመውን ድብደባና ስቃይ ካሰራጨ ቦኋላ የሊባኖስ መንግሥት በአሰሪዋ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ በይፋ ገልጾ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ካሪታስ የሚባል የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የሰብ አዊ እርዳታ ሰጪ ድርጅት ተጎጂዋን ወጣት ለማሳከም ሆስፒታል ያስገባት ቢሆንም በህክምና እርዳታ ላይ በነበረቺበት ክፍል ውስጥ በትናንትናው ዕለት ጠዋት በተኛችበት አንሶላ እራሷን አንቃ እንደገደለች ተዘግቦአል።

ይህ በዚህ እንዳለ የወያኔ ኢፍትሃዊ ሥርዓት በፈጠረው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተማረው ና ተስፋ ቆርጠው ወደ ውጪ ለመውጣት ሲጓዙ የነበሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተጫኑበት ሁለት ተሽከርካሪዎች ሱማሌ ላንድ ውስጥ ተገልብጦ ማለቃቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

*በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን አሰከፊ ኑሮ እና ጭቆና ለመገላገል በርካታ ኢትዮጵያውያን በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ አገር ጥለው እየተሰደዱ እንደሆነ ሲታወቅ በግብጽ አድርገው ወደ እስራኤልና ወደ አውሮፓ ለመሄድ የሚሞክሩ ስደተኞች በሲና በረሃ ውስጥ እየታገቱ የሆድ እቃቸው እየወጣ ለገበያ እንደሚቀርብ በቅርቡ ሲኤን ኤን እና አንድ የአውስትራሊያ ቴሌቪዥን ይፋ ማድረጋቸው ይታወሳል።*

ይህ ሁሉ ስቃይ በኢትዮጵያዊያኑ ላይ እየደረሰ ባለበት ሰ ዓት ዘረኛው የመለስ አገዛዝ ሌላ 30 000 ሴቶችን ወደ ሳውዲ አረቢያ ለመላክ በዝግጅት ላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

## በጋምቤላ ተማሪዎችን ይዞ ይጓዝ በነበረው አውቶቡስ ላይ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የሸጠላቸውን ባዕዳን ዕላማ ማድረጉን ለማዘናጋት የራሱን ጸጥታ ሰራተኞች በማሰማራት ይህንን የመሰለ ዘግናኝ እርምጃ ለመውሰድ ችሎአል በማለት እያማረሩ ያሉ የክልሉ ነዋሪዎች ወያኔ በትግራይ በረሃ በነበረበት የትግል ወቅት ህዝቡን በደርግ ላይ ለማሸፈት ሆን ብሎ የተሳሳተ መረጃ በማቀበል ሃውዜን ውስጥ ለገቢያ በተሰበሰበው ህዝብ ላይ ያንን የመሰለ ዘግናኝ ጭፍጨፋ በማስፈጸም የትግራይን ህዝብ ለእኩይ አላማው ከጎኑ ለማቆም ችሎ እንደነበር በምሳሌነት ይጠቅሳሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ ማንነታቸው ያልታወቁ ታጣቂዎች ላለፉት 3 ወራት በክልሉ እያካሄዱት ያለው ግዲያ ያሰጋቸው በጋምቤላ ነዋሪ የሆኑ የመሀል አገር ሰዎች ተመሳሳይ ጥቃት ይፈጸምብን ይሆናል በሚል ስጋት አካባቢውን ለቀው መውጣት መጀመራቸውን ተያይዞ የደረሰን ዜና አመለከተ።

ባለፈው ሰኞ ወደ ጋምቤላ ይጓዝ በነበረው አውቶቡስ ላይ ጥቃት ከተፈጸመ ቦኋላ በርካታ የወያኔ ፌደራልና የመከላከያ ሰራዊት አባላት ጋምቤላ ውስጥ የሰፈሩ ሲሆን፣ በየትኛውም የከተማው መውጫ እና መግቢያ በሮች ከፍተኛ ፍተሻዎችን እያደረጉ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ኢሳት በትናንትናው ዜና ዘገባው እንደገለጸው ወያኔ ሰራዊቱን በጋምቤላ ከተማ ውስጥ ካሰፈረ ካለፈው ማክሰኞ 11 ሰአት ጀምሮ ዘገባውን እስካቀረበበት ትናንት ድረስ በጋምቤላ ከተማ የሚኖሩ የአኝዋክና የኑዌር ተወላጆች ወያኔ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለጽ ከቤት ውጪ አልታዩም ብሎአል። የአካባቢው ተወላጆች ቤታቸውን ዘግተው መቀመጥ ባለሥልጣናቱን ጋራ እንዳጋባም ገልጾአል።

ወያኔ ላለፉት 20 አመታት በህዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለው በደልና ስቃይ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል እያስከፋ መሆኑ በዚህም ምክንያት ወያኔ ባልታሰበ ሰዓትና ቀን ሊፈነዳ በሚችል ፈንጂ ላይ እንደተቀመጠ ብዙዎች ይናገራሉ።

ግንቦት 7 የዘረኛውን ወያኔ አገዛዝ እድሜ ለማሳጠር ሁሉም ተባብሮ እንዲነሳ ጥሪ ከማስተላለፍ በተጨማሪ የአገሬ ጉዳይ ይመለከተኛል ከሚሉ ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ጥምረት በመፍጠር የህዝቡን የነጻነትና የፍትህ ጥማት ከግብ ለማድረስ እየታገለ መሆኑ ይታወቃል።

## ጥምረትና ኦነግ የተሳተፉት ደማቅ ህዝባዊ ስብሰባ በኖርዌይ ዋና ከተማ ኦስሎ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

"ትብብር ለምን? ከማን ጋር መተባበር ይበጃል?" እና የመሳሰሉ ጉዳዮች አንስተው መርምረዋል። ትብብር ማድረግ ለምን አስቸጋሪ እንደሆነም ሰፋ ያለ ገለፃ አድርገዋል። ትብብርን በሚመከት የድርጅታቸው ግንቦት 7ን አቋም አብራርተዋል። ዶ/ር ታደሰ ብሩ በጄኔራል ከማል ገልቹ ከሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ለወሰደው ደፋር አቋም ያላቸውን አድናቆች ገልጸዋል። በመጨረሻም በቀጣይ በአጣዳፊ መከናወን አለበት ያሉትን የሲቪል ማኅበራት ኅብረት አስፈላጊነት ላይ አጽንዖት ሰጥተዋል። እንደ ዶ/ር ታደሰ ገለፃ፣ ኢትዮጵያ አገራችን "በነፃ ተቋማት ድርቅ" ተመታለች። ወያኔ አገር ቤት ውስጥ የነበሩትን ሲቪል ማኅበራት አፍርሶ ወይም ጠልፎ ጨርሶ ፊቱን ወደ ዲያስፖራ ማዞሩ አትተው፤ አፋጣኝ ርምጃ ካልተወሰደ በስተቀር ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተደረገ ሁሉ በውጭ አገራትም የሚገኙትም ሲቪል ማኅበራት መጠለፋቸው አይቀርም በማለት የችግሩን ስፋትና አሳሳቢነት አመላከተዋል። በመጨረሻም ሲ.አር.ዲ.ኤ ለእርዳታ ድርጅቶች እንዳደረገው ዓይነት የሲቪል ማኅበራት ኮንሰርተም እንዲቋቋም ጥሪ አድርገዋል።

ከስብሰባው ተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። በርካታ ተሰብሳቢዎች በግንቦት 7 ራዕይና ስትራቴጂ ላይ ማብራሪያ እንደሰጣቸው ጥያቄዎችን አቅርበው ምላሽ አግኝተዋል።

በመጨረሻም የስብሰባው አዘጋጅ ኮሚቴ ተወካይ ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለዲሞክራሲ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋር ለተሰብሳቢዎች የሰጡት ገለጻ እጅግ አርኪ እንደሆነ ገልጸው ወያኔ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም እንዲቻለው በተለይ በኦሮሞውና በአማራው መካከል ለመገንባት የተሞከረውን የመለያየ ግንብ ለመስበር የሚያስችል እርምጃ በመወሰዱ ሁላችንም ድስተኞች ሆነናል በዚህም የተነሳ ሁላችንም ከአሁን ቦኋላ ኦሮሞዎችም፤ አማሮችም፤ ትግሬዎችም፤ ካንባታዎችም፤ ሱማሌዎችም ፤ አፋሮችም ወዘተ የሆን የአንድ አገር ህዝብ ነን። የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ዳግም አይለያየንም በማለት በታደሰ የአንደነት መንፈስ ስብሰባውን ዘግተዋል።

በተያያዘ ዜናም በዚያው በኖርዌይ የሚኖሩ ስደተኞች ትላንት ሰኞ መጋቢት 3 ቀን የኖርዌይ መንግስት ከዘረኛዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር ኢትዮጲያዊያን ስደተኞችን በሀይል ለመመለስ የተፈራረሙትን ዉል በመቃወም ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ አካሄዱ። ቁጥራቸዉ ወደ 400 የሚጠጉ እነኚሁ ስደተኞች ባኦስሎ ከተማ ከሚገኘዉ ትለቁ ማኢከላዊ አደባባይ ተነስተዉ የህገራቷ ፓርላማ ጽ/ቤት ፊትለፊትና በፍትህ ሚኒስተር በመገኘት አቤቱታቸዉን ለየተወካዮቹ አቀርበዋል። በጉዟቸዉም የተለያዩ መፈክሮችን ሲያሰሙ ከነበሩት ዉስጥ መለስ ገዳይ ነዉ. መለስ የዘር አጥፊነት ወንጀለኛ ነዉ. ወደ ግዳዮች አትመልሱን፣ የኢትዮጵያን ነፃነት በትግላችን እንቀዳጃለን የኖረዌይ መንግስት አላፊ ፓረቲን ሳይሆን ህዝብን ይርዳ. ዝረኛንና አመባገነንን መንግስትን መርዳት ጥፋት ነዉ. የመሳሰሉትን በደመቀ ሁኔታ ሲያስተላልፉ ነበር።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz**

**አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz**

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org